# የአጎስቲኖ ታሪክ

# Agostino’s story

LIDA Italia

Billie Cejka Risnes

Loza Tadesse Mamo

5

አማርኛ am / English en

ስሜ አጎስቲኖ ይባላል 51 ዓመቴ ነው። ስራዬ በብስክሌት ምግብ ማድረስ ነው። ሁለት ሴት ልጆች አሉኝ ግን ብዙም ኣናወራም። እኔና እናታቸው አብረን አንኖርም ምክንያቱም ተፋተናል።

• • •

My name is Agostino and I am 51 years old. My job is delivering food by bicycle. I have two daughters, but we hardly ever speak. Their mother and I no longer live together because we are divorced.

ከፍቺ በኋላ የቤት ኪራይ መክፈል ስለማልችል ከእናቴ ጋር ነው የምኖረው። በዚህ ከተማ ውስጥ ኪራይ በጣም ውድ ነው።

• • •

I live with my mother, as I cannot afford to pay rent after the divorce. Rent is very expensive in this city.

ከጥቂት ወራት በፊት በአንድ ኩባንያ ውስጥ በጽዳት ሠራተኛነት እሠራ ነበር። የተበላሹ ነገሮችን አስተካክያለሁ፣ ሳጥኖች እሸከማለው እና ማንም በፈለገው ጊዜ እረዳ ነበር። አንድ ቀን ድርጅቱ አባረረኝ። ለምን እንደሆነ አልገባኝም።

• • •

A few months ago I was working as a janitor for a company. I repaired things that were broken, carried boxes, and helped when anyone needed it. One day the company fired me. I did not understand why.

ብዙ ሰዎች በብስክሌት ምግብ ሲያቀርቡ አየሁ። ብስክሌት መንዳት ስለምችል የአንድ ትልቅ ማጓጓዣ ድርጅት በር አንኳኳሁ። ለእያንዳንዱ ማድረስ ሦስት ዩሮ ሰጡኝ። በቀን 40€ አገኛለሁ። በጣም እድለኛ ከሆንኩ 60€ እና ደንበኞቼ የኪስ ይሰጡኛል።

• • •

I saw many people delivering food by bicycle. I can ride a bicycle, so I knocked on the door of a big delivery company. They offered me three euros for each delivery. I make 40€ per day, 60€ if I am very lucky and the customers tip me.

የበዓል ቀን ክፍያ የለም፣ ስትታመም ክፍያ የለም፣ ባጠቃላይ ምንም አይነት መብት አላገኘሁም። ትክክል አይመስለኝም ግን ስራውን እፈልጋለሁ። አብዛኛዎቹ ሌሎች ሰራተኞች ከመላው አለም የመጡ ስደተኞች ናቸው።

• • •

I get no paid holiday, no sick pay, hardly any rights at all. I do not think that is right, but I need the job. Most of the other employees are immigrants from all over the world.

ብዙ የዴሊቨሪ ሠራተኞች በየቀኑ በአደጋ ይጎዳሉ። ከዚያም አንድ የ25 ዓመት የዴሊቨሪ ሠራተኛ በመኪና ተገጭቶ ሲሞት ባለ ሥልጣናቱም እኛን ልብ ማለት ጀመሩ። ይህ ከመሆኑ በፊት መሞቱ አሳፋሪ ነው።

• • •

Many delivery people are injured in accidents every day. Then, when a 25-year-old deliveryman was hit by a car and died, the authorities started noticing us. It is a shame he had to die before that happened.

ከሌሎች ኩባንያዎች ከመጡ ሰዎች ጋር በመሆን ከአካባቢው ዩኒየን ጋር ስለሠራተኞች መብት ኮርስ ወሰድኩ። የሕግ ምክር በነጻ ሰጡን። የበለጠ እውቅና እና መብት ለማግኘት ታግለናል።

• • •

Together with delivery people from other companies, I took a course on workers’ rights with a local union. They offered us legal advice free of charge. We struggled to get more recognition and rights.

ከረዥም ጊዜ በኋላ ድካማችን ሁሉ ፍሬያማ ሆነ። አንድ ትልቅ የዴሊቨሪ ድርጅት ከፍተኛ ቅጣት መክፈልና ለሠራተኞች ቋሚ ሥራ መስጠት ነበረበት። በአለም ውስጥ በየትኛውም ቦታ ሲከሰት ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር። ነገሮች መሻሻል የጀመሩ ይመስላል።

• • •

After a long time all our hard work paid off. One big delivery company had to pay a huge fine and to give workers permanent jobs. It was the first time that had happened anywhere in the whole world. It looks like things are starting to improve.

# LIDA Stories

lidastories.net

## የአጎስቲኖ ታሪክ

## Agostino’s story

LIDA Italia
Billie Cejka Risnes
Loza Tadesse Mamo (am)

CC BY